የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

# **ድርጅታዊ መግለጫ**

ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) 3ኛ ድርጅታዊ ጉባኤውን በኔዘርላንድ ደንሃግ ከተማ ከመጋቢት 2 እስከ 5, 2007 የፈረንጅ ኣቆጣጠር በተሳካ ሁኔታ ኣካሂዷል።

ይህ ጉባኤ ኣገራችን ኢትዮጵያ ኣሁን የምትገኝበት ሁነታ ከምንጊዜም የከፋና ኣሳሳቢ ለመሆኑ ተመልክቷል። የረሃብ መደጋገም፣ የተላላፊ በሽታዎች መስፋፋትና፣ በክስተት ላይ ያለው የፖለቲካ ቀውስ ጉባኤው ኣንስቶ ከመረምራቸው ጉዳዮች ከፊሎቹ ነበሩ።

ኣገራችን የምትገኝበትን ኣጠቃላይ ቀውስና ውስብስብ ከዓለም ኣቀፋዊና ዞናዊ እንደዚሁም ኢህአደግ ከሚከተላቸው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች አንጻር በጥልቀት በመመርመር ት.ዴ.ት ችግሮቹን የሚቀርፍበት የትግል ኣቅጣጫ ቀይሷል።

በግንቦት 2005 የተካሄድው ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ለድምክራሲ ያለው ጥማትና በኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ ላይ ያለውን ጥላቻ ቁልጭ ብሎ ኢንድታይ ማድረጉና የለውጥ ፍላጎቱም በምንም ዓይነት ሃይል ሊታፈን እንደማይችል ጉባኤው ኣስምሮበታል። ኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ ሽንፈቱን ላለመቀበል በህዝቡና በተቃዋሚዎች ላይ የሚያደርገውን ሽብርና ወከባ፣ እስርና ግድያ ጉባኤው ኣውግዟል። ኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ እድሜውን ለማራዘም ሲል ለትውልድ ሊቀር የሚችል ቅራኔዎችን እንደ ዘርና ሃይምኖት የመሳሰሉትን ጥላቻዎች እንዲቀሰቀሱና ህዝብ እርስበርሱ እንዲጋጭ እያደርገ መሆኑን ጉባኤው ተገንዝቧል።

ኣሁን ላለው ፖለትካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ዋናው ተጠያቂ በስልጣን ላይ ያለው ኣምባገነኑ የኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ መንግስት መሆኑንና በስልጣን እስካለ ድረስም ሁኔታው እየተባባሰ እንደሚሄድ ጉባኤ ኣስምሮበታል። በህዝቡ መካከል የተፈጠረው ኣስነዋሪ መከፋፈል ኣገሪቱን የጽንፈኞች መነሃሪያ ሊያደርጋት እንደሚችል የትግራይ ደሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) ስጋቱን ሳያሰምርበት ኣላለፈም። ይህ ለኣገሪቱ ኣደገኛ የሆነ ጉዞ እንዲቆምና የችግራችን ምንጭ ምን እንደሆነ አውቀን ለጋራ እርባና ሲባል በህብረት በመደማመጥና በመከባበር በሃቀኛ ልጆችዋ መካሄድ ያለበትን የትግል ዘዴና የግኙኝነት መልክ በመቀየስ የመፍትሔ ኣቅጣጫ ጠቁሟል።

የትግራይ ህዝብ እንደማንም ኢትዮጵያዊ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ኣገዛዝ ስር እየማቀቀ ያለ እንጂ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ኣመራርና ካድሬዎች ይሁኑ ኣንዳንድ በጽንፈኛ ኣመለካከት ወይም የህዝቡን ሁኔታ ጠለቅ ብለው ያልተገነዘቡ የዋሆች እንደሚሉት የደላውና መብቱ የተከበረለት ህዝብ ኣለመሆኑን ት.ዴ.ት ያረጋገጠል። በትግራይ ተሰሩ የሚባሉት መንገዶች ይሁኑ ፋብሪካዎች የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መሪዎችና ኣጫፋርዎች ኪስና ሆድ የሚያሳብጡ ተቋሞች እንጂ ኣብዛኛው የትግራይ ህዝብማ የእለት ምግብ ኣጥቶ የሚንከራተትና 'በምግብ ለስራ' የልመና ስንዴ ከርታታ ኑሮ የሚገፋ መሆኑን ነው የምንመለከተው። የትግራይ ህዝብ ከዚህ ችግርና ኣፈና ለመውጣት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን እንዲታገልና እንዲሳካለት መተባበር እንጂ ከኣምባገነኖች ሰልፍ ኣስገብቶ ጭቁኑን ህዝብ መውቀጡ የትም የማያደርስ የጨለምተኝነት ጉዞ መሆኑን ት.ዴ.ት ያሳስባል። በተጨማሪም ህዞቦችን የሚያጋጭ ኣመለካከትና ኣሰራር የኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ኣምባገነናዊ ስርኣት ዕድሜ እንዲራዘም ኣስተዋጽኦ ስላለው ይህ ኣይነቱ እንቅስቃሴ ባስቸኳይ መቆም ኣለበት እንላለን።

የተቃዋሚ ድርጅቶች የጋር ትግልን በሚመለከት፣ ተቃውሚዎች ድርጅታዊ ጥቅምን ከኣገር ጥቅም በማስቀደም ትግሉን በመጥለፍ የሚፈለገውን ውጤት ልያስመዘግብ እንዳልቻለ ጉባኤው ተገንዝቧል። ት.ዴ.ት ኣሁንም በድጋሚ ከድርጅት ጥቅምና ክብር ይልቅ የኣገርን ጥቅምና ክብር በማስቀደም ለተነሳንባቸው ህዝባዊ ኣላማዎች መሳካት በጋራ መታገሉ ኣማርጭ የማይገኝለት የትግል ኣቅጣጫ መሆኑን ኣበክሮ ያስገነዝባል። ኣልፎ ኣልፎ በቁጣና በጥላቻ ብቻ እየተገፋን ያለ ሁነኛ ጥናት ዘልቄታ በሌለው መንገድ የሚካሄደው የትግል ትርምስ የትም የማያደርስና ለትግላችንም ኣደፍርሽ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይኽ ካልታረመ ደግሞ ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ማንሰራራት ኣስተዋጽኦ እንደሚኖረውና ትግላችንን እንደሚጎትተው ግልጽ ነው። የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት.ዴ.ት) ለህብረት ትግል መሳካት የተፈለገውን መስዋእት ለመክፈል ቃል ይገባል።

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ

TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

ድርጅታችን ዴሞክራሲያዊ ኣመለካከት ካላቸው ብሄራዊና ህብረ-ብሄራዊ ድርጅቶች ጋር በመሆን ሊፈጠር ወደሚችል ሃገርዊ ድርጅት በህብረት ብቻ ሳይሆን ወደ ውህደት ለመሸጋገርም ፍላጎት እንዳለውና ዝግጁ እንደሆነም ያረጋግጣል።

ኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ ከጎረቤት ኣገሮች ጋር የሚጭረውን ጠብ ጉባኤው በኣንክሮ ተመልክቶታል። በቅርቡ ኢ.ህ.ኣ.ደ.ግ በሶማሊያ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ደንበር ጥሶ ሶማልያን መውረሩ ት.ዴ.ት ኣጥብቆ ይኮንነዋል። ከኤርትራ ጋር ያለው ግጭትም በመሰረቱ በሁለቱ ኣምባገነን መሪዎች የተጫረና የኢትዮጵያንም ይሁን የኤርትራን ህዝቦች ጥቅም የማይወክል መሆኑን በማመን ኣሁንም በድጋሚ የሁለቱም ኣምባገነን መሪዎች ጠብ ጫሪነት እንኮንነዋለን። ሆኖም ግን በኢትዮጵያና ኤርትራ ዘላቂ ሰላም እንዲኖር የኢትዮጵያን የባህር በር መብትና የግዛቷ ላእላውነት የሚጠብቅ ስምምነትና ውል መደርግ ኣለበት ብሎ ጉባኤው ኣስምሮበታል። ኢትዮጵያ ከ80 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ያላት ትልቅ ኣገር ከመሆኗም በላይ በታሪካዊ ሂደቷ ሁልጊዜ የባህር በር የነበራት ኣገር በመሆንዋ <u>የባህር በር ይገባኛል</u> መብትዋም መከበር ኣለበት እንላለን።

በመጨርሻ ጉባኤው ድርጅቱ እስካሁን ያከናወናቸውን ስራዎችና ግኑኝነቶች እንዲሁም ውስጣዊ ኣሰራሩን በጥልቀት ገምግሞ በኣሰራሩ ይሁን በቅርጽ መደረግ ያለበትን መሻሻልና ተገቢ የስራ መደቦችን በመተለም እንዲሁም የድርጅቱን ኣመራር በዴሞክራሲያዊ ኣገባብ በመምረጥ ስብሰባውን ኣጠቃሏል።

## <u>የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!!</u>

ለዲሞክራሲና ለፍትህ ያለህን ጥምና ምኞት በግንቦት 2005 ምርጫ ላይ በማያዋላዳ መንገድ ማሳየትህን የሚዘነጋ ኣይደለም። ኣምባገነኑ የመለስ መንግስት ግን ያገኘሽውን ድል በጠራራ ጸሓይ በመቀማት የመረጥካቸውን መሪዎችህ በእስርና በማንገላታት፣ ኣንዳንዶችንም በመግደል፣ ህዝቡንም በማሸበርና በገፍ በማሰር ተደጋጋሚ ግፍ እየፈጸመብህ መሆኑ ግልጽ ነው። የኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ ግብዝነት የህዝቡን ማዕበል በኃይል የሚመለስ እየመሰለው ትግልህ በጠነከረ ቁጥር የሚሰጠው ምላሽ የበለጠ ኃይል መጠቀምን ነው። ይህም ከህዝቡ ጋር ያለውን ቅራኔ በይበልጥ የሚያጠናክርና የትግሉንም ጥንካሬ እንዲጎለብት የሚያደርግ ነው። ይህንን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ትግልህ የበለጠ መስዋእትነትና ኣደርጃጀት እንደሚጠብቅብህ ለማስገንዘብ እንወዳለን። በዚሁም ኣጋጣሚ የታሰሩት መርዎቻችንና ሁሉም የኅሊና እስረኞች ያለምንም ቅድመሁኔታ እንዲፈቱ እንጠይቃለን።

## <u>የኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ መሪዎችን ለስልጣን ያበቃሃቸው ሰራዊት ሆይ!!</u>

ያካሄድከው ትግል ለህዝብ ኣንድነትና እኩልነት፣ ለመብት መከበርና ለተሻሻለ ኑሮ እንደነበር ኣይሳትም። ይሁን እንጂ የኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግ መሪዎች ያ ሁሉ ቃልና የከፍልከውን መስዋእትነት ረስተው በስልጣን ከለላ እየባለጉ ነው። ህዝባችንን ለመከራ ዳርገው ኣፍነው እርስበርሱ ሲያናክሱትና ኣንድነቱን ሲያጠፉት ዝም ብለህ መመልከት ኣይገባህም። ለኢትዮጵያ ህዝብ ዘብ ቁም። የኢትዮጵያ ህዝብ ኣገልጋይ እንጂ የኢ.ህ.ኣ.ደግ ትእዛዝ ኣክባሪና መሳርያ እንዳትሆን ህዝባዊ ጥሪ እናቀርብልህ ኣለን።

## <u>ዴሞክራሲያውያን የተቃውሞ ድርጅቶች ሆይ!!</u>

ህዝባችን በኣምባገነኖች ታፍኖ በችግር እየተጠበሰ ኣንድነቱ ሲጠፋ ልጆቼ መጡልኝ እያለ የተሰፍ እጁን በዘረጋበት ወቅት ድርጅትን በማስቀደም በእልህና ፉክክር እርስበርስ ከመጠላለፍና የኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግን ዕድሜ ከማራዘም ለህዝባችንና ኣገራችን ጥቅምና ክብር ስንል ልዩነትን ኣጣጥመን በጋራ ወድፊት መራመድ ኣለብን እንላለን።

በእኩልነትና በመከባበር የተመሰረተች
ጠንካራ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንገነባለን!!!

ት.ዴ.ት
መጋቢት 9, 2007